ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)
Website: www.moreshwegenie.org   E-mail: infoandpr@moreshwegenie.org

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት*  *እሑድ ሰኔ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፩ዓ.ም.*  *ቅጽ ፯ቁጥር ፲፩*

# ዐማራው ከፊቱ የተጋረጠበትን የወቅቱን ፈተና ለመወጣት አንድነቱን ማጠናከር አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው!!

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም. የዐማራ ርዕስ መስተዳደር መቀመጫያ በሆነው በባሕር ዳር ከተማ የርዕሰ መስተዳድሩ ጽህፈት ቤት የተፈጠረውን ሁከትና ውጤት አስመልክቶ በወጡትና እየወጡ ባሉት ዜናዎች እጅግ ክፍተኛ የሆነ ሐዘን ተሰምቶናል። መዘዙም እንዲህ በቀላሉ የሚያባራ እንዳልሆነ ሕዝባችን በውል ጠንቅቆ የሚገነዘብ መሆኑን አንጠራጠርም።

የዚህ አስደንጋጭና የመላው ዐማራን ህዝብ የማንነት ጥያቄ ፤የነጻነትና የህልውና ትግል ተጋድሮት፤እንዲሁም ተደራጅቶ ራሱን የመጠበቅ አቅሙን የመፈታተን ጎጂ የሆነ ተግባር ላይ ዜናዎችና ተጨባጭ መረጃዎች ደረጃ በደረጃ እየወጡ ሲሆን በድርጅታችን በኩል ተገቢውን የዐማራውን ትግል አቅጣጫና ቀጣዩን የትግል ስልት በዝርዝር ተከታታይ የማስተማሪያና የማንቂያ መግለጫዎችን እናውጣለን። በስሌትና በታቀደ ሁከት የተፈጸመው ድርጊት ከእነውጤቱ በዐማራው ሕዝብ ላይ የተቀነባበረ ሴራ እዬተካሄደ መሆኑንና መኖሩን የሚያመላክት የመጨረሻ ደወል ሰለመሆኑ ዐማራው በሚገባ የሚረዳው ነው።

በሕዝባችን ላይ የተጋረጠውን የህዝባችንን ሉዐላዊነትና እራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ተቀናቃኝ አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ የዐማራው ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የዐማራው የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ንቅናቄዎች፤ሲቭክ ድርጅቶች ፤ የሙያ ማህበራት እና ድፈን የዐማራ ሕዝብ በሙሉ በመካከላቸው ያለውን ጥቃቅን ልዩነቶች ወደጎን በመተው ከምንጊዜውም በላይ አንድነትን ማጠናከር አማራጭ የሌለው ግዴታችን ነው።

ፈለገ አሥራት የትግላችን መመሪያ ነው!!!

ዐማራው አንድነቱን ከአጠናከረ የሚደፍረው ምንም ሀይል አይኖርም!!!

ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥላል!